# ★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ቅጽ 42 ቁ.1 መስከረም 2009 ዓ.ም

## መስከረም ሲጠባ ሕዝባዊ ትግሉ ጎመራ

አዲስ ዓመት እኛ ኢትዮጵያዊያን በሐዘንም ሆነ በደስታ በአንድነት የምንቆምበት፤ የፅናታችን፤ የመተሳሰብ፤ የመከባበርና የመቻቻል ባህላችን፣ ኢትዮጵያዊነታችን ከአፅናፍ እስከአፅናፍ የሚገለፅበት ክቡር ፀጋ ሆኖ ለረጅም ጊዜ የቆየ ሲሆን የዘንድሮም ወርሃ መስከረም ይህንን በተግባር አሳይቷል። ታሪክም ዳግም በትውልድ መታደሱን በገቢር አስመስክሯል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬም እንደትናንትናው የዘር ሐረግ ሳይቆጥር፤ ሃይማኖትና ፆታ ሳይገድበው፤ የሰማዕታቱን ባለአረንጓዴ ቢጫና ቀይ ቀለሙን ሰንደቅ ከፍ አድርጎ፤ የኢትዮጵያዊነት ወኔን ተላብሶ፤ ጎጠኞችንና አምባገነኖችን በትግልና በደሙ አጋልጧል።

ለእኛ ኢትዮጵያዊያን በመካከላችን የሚታየው የቋንቋ፣ የባህልና የእምነት ልዩነት ዓይነቱ ለበዛና ወጥነቱን (ኢትዮጵያዊነቱን) ለጠበቀ ድንቅ የፈጠራና የባህል መሠረት በመሆኑ አጅግ የምንኮራበት ጌጣችንና ሀብታችን እንጂ የምናፍርበት ሰንክ ከቶም ሆኖ አያውቅም።

እኛ ኢትዮጵያዊያን በመላው ዓለም የምንታወቅበት፤ በመልካም የምንነሳበትና የምንከበርበት፤ በነፃነት ወዳድነታችን፣ በአትንኩን ባይነታችን፣ በረጅሙ አኩሪ ታሪካችን፣ በጀግንነታችን፣ በሰው አክባሪነታችን፣ ያሸበረቀ ባህል ባለቤት በመሆናችንና ተፈታታኝ የሆኑ መሰናክሎችንና እክሎችን በፅና አንድነት በመቋቋማችን እንደሆን ይታወቃል።

ይህ ዥንጉርጉር ባህላዊ ህብረ ቀለም ደግሞ ኢትዮጵያዊያንን ከዳር እስከዳር አስተሳስሮን፤ ፍቅር አላብሶን፤ ዓይንና ቀልብን አድምቆ አሸብርቆን፤ ሀገራችንም በነዚህ ህብረ ቀለማት አሸብርቃና ደምቃ፤ የውስጥ ቀርቶ የውጭውን ዓይንና ቀልብ እንድትስብ አድርጓት የቆየ እንጂ፤ ለመነጣጠልና ለመከፋፈል ምክንያት ሆኖም አያውቅም። ለዚህ ዓለምን ያስደነቀ አንድነቱ ታሪካዊ ምስክር የሆነውና ለዘረኞች ሁሉ የራስ ምታት ሆኖ የሚኖረውሐቅ፤ አፍሪካን በቅኝ ግዛት ተቀራምተው የተፈጥሮ ሃብቷን ብቻ ሳይሆን ህዝቧንም አረመኔያዊ ለሆነው ባርነት በገፍ ያጋዙ ቅኝ ገዥዎች ኢትዮጵያ ላይ ሲደርሱ፤ ዜጎቿ ጎሳ፣ ሃይማኖትና ቋንቋ ሳይሉ

አንድ አገር አንድ ህዝብ ሆነው በመቆም ጠላቶቻቸውን አንድ በአንድ ሃፍረትን እያከናነቡ መመለሳቸው ነው።

ከታሪክ መማር እንደሚቻለው ጽኑ አንድነት የሌለው ሕዝብ፤ የደመቀ ታሪክና ባህል ሊኖርው አይችልም። ጽኑ አንድነት የሌለው ሕዝብ አገሩንም ሆነ ድንበሩን፣ ነፃነቱንም ሆነ መብቱን፣ ሊያስከበር ከቶም አይችልም። እንዲህ አይነቱ የፀና አንድነትና አገራዊ ቀናኢነት ሊመጣ የቻለው መልካም አስተዳደር ሰፍኖ የሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት ተከብሮ፤ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሁለመና ገፅታቸው ተከብረው ሳይሆን ሕዝብ ለዘመናት አብሮ በመኖር በመዋለዱ፣ በመተሳሰቡና በመተሳሰሩ የተነሳ ለመሆኑ የበርካታ ሀገሮች ተመክሮ የሚያመላክቱት ነው።

ከሁሉም በላይ እኛ ኢትዮጵያዊነት ስንል፤ ጠባብ ብሔረተኞች እንደሚያላዝኑት፤ አንዱን ክፍል ለመጥቀም ሌላውን ለመጨቆን ወይም ደግሞ አንደ ትምክህተኞቹ የህዝብን፣ መብትና እኩልነትን ረግጦ ቁንፅል ታሪክን ማነብነብ ወይም ግልብ አንድነትን መስበክ ሳይሆን ለሀገር፣ ለህዝብ፣ ለወገን፣ ለሀገራዊ ባህልና ቁሳዊ ቅርሶች፤ ለነፃነትና ፍትህ፣ ለዴሞክራሲያዊ መብቶች ተቆርቋሪነት ማለታችን ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያን ሕዝብ የረጅም ጊዜ ታሪክ ስንመረምር ሕዝብ በታሪኩ ውስጥ አንድነቱን/ኢትዮጵያዊነቱን ጥያቄ ውስጥ አስገብቶ አያውቅም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን በጋራ ሲጠብቅና ሲያስጠብቅ የኖረ ኩሩና ጀግና ህዝብ ነው። ኢትዮጵያዊ ማለት ደግሞ ሁሌም በወቅቱ መልካም ናቸው ብሎ በተቀበላቸው እሴቶቹ ላይ በመመስረት ለሀገሩና ለነፃነት ክብሩ ከምንም በላይ ቅድሚያን የሚሰጥ፤ ስለሀገሩ፣ ስለድንበሩ ስለታሪኩና ስለባህሉ በውል የሚያውቅና የሚቆረቆር፤ ሀገር ምን ያህል ዋጋ እንዳለው በውል የሚረዳ፤ ሀገሩንና ክብሩን ለባእዳን ሀይሎች አሳልፎ መስጠትን ቀርቶ ይህን ማሰብን እንደ ውርደት የሚቆጥር ኩሩና ጀግና ህዝብ ማለት ነው።

በአንዳንድ የታሪክ አጋጣሚዎች እንኳን ሀገሩ አደጋ ላይ ወድቃ በተገኘችበት ወቅት ፈጣን ምላሽ በመስጠት ሀገሩን ለማዳን፤ ወገኑን ለመታደግ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል ለደቂቃም የማያመነታ፤ በእምነቱና በቃል ኪዳኑ ፀንቶ የሚገኝ፤ ሁኔታዎች በተለወጡ ቁጥር ተስፋ መቁረጥን የማያውቅ፤ በማንነቱ የሚኮራና በቀላል ውዥንብር የማይፈታ መሆኑን በተግባር ያስመሰከረ ኢትዮጵያዊ ወኔን የተላበሰ ህዝብ ነው።

ዛሬ ላይ ቆመን ያለፉትን መስከረሞች ስንቃኝ፤ መጪውንም አዲስ ዓመት ስናማትር ስለ እውነት፣ ስለ ሀገር ፣ ስለ ሰንደቅ ዓላማ፣ ስለ ሕዝብ፣ ስለዘላቂ ሰላምና ፍቅር ነበር ያለፉት ጀግኖቻችን የማይናወጥ ቃል ኪዳናቸውን መመሪያቸው አድርገው ሀገራቸው የጠየቀቻቸውን መስዋዕትነት በጀግንነት የከፈሉት። ዛሬ የዚህ ታሪክ፤ የዚህ ባህልና ቅርስ ባላቤቶች ነን እያልን ልንኮራባቸው የቻልነው በዚሁ በአርበኞቻችን በተከፈለው ከፍተኛ መሰዋአትነት የተነሳ ነው።

ዛሬም የዚችን ታላቅ ባለታሪክ ሀገር ሉዓላዊነት የማስከበር፤ የዚህ ኩሩ ህዝብ አንድነቱ በዜጎች እኩልነት ተጠብቆ እንዲቀጥል የማድረግ ፤ የሕግ የበላይነት ተከበሮ፤ ዜጎች በእኩልነት የሚኖሩባት አገርን እውን አድርጎ የማስቀጠል ታሪካዊ ሀላፊነት የወደቀው "ያ ትውልድ" ተብሎ በተሰየመውና በቀጣዩ ትውልድ ትከሻ ላይ ነው። ሀገርም እንደ ሀገር ልትቀጥል የምትችለው ታሪኩን ያልዘነጋ፤ ማንነቱን በትክክል

መገንዘብ የቻለ፣ በአገሩ ሉዓላዊነትና በኢትዮጵያዊነቱ ላይ ፍፁም የማይደራደር ትውልድ/ዜጋ ሲኖር ብቻ ነው። እናም ይህ የአሁኑ ትውልድ አይለጉት ግዳጅ ከፊቱ ተደቅኖበት ይገኛል።የአገርን ህልውናና የዜጎችን አንድነት የሚፈታተኑ አግጠውና አፍጠው የሚታዩትን አበይት አገራዊና ሕዝባዊ ችግሮችን በሚገባ አበራይቶና ለይቶ በማጤን፤ ለአገርና ለህዝብ ይበጃል ተብሎ በህዝብ የታመነበትን የጋራ ዓላማ ተግባራዊ/ዕውን የማድረግ ታሪካዊ ግዳጅ ተጥሎበታል።ይህ ሳይሆን ቀርቶ ኅጠኝነት በሀገራችን ምድር ከነገሰ ያለፈው ታሪካችን የወደፊት ተረት፣ የአገራችንም መልከዓ ምድር ተቀይሮ ዳሩ መሀል፤ መሀሉ ዳር የማይሆንበት ምክንያት የለም። ዛሬ ያለው በአገርና በህዝብ ላይ የተሰነቀረ ወያኔያዊ ጋሬጣ ወይም የተቃጣው አደጋ የሚያሳየንም ይህንኑ ሐቅ ነው።

ለዚህም ነበር ኢሕአፓ ገና ጀንበር ሳትጠልቅ በጠዋቱ፣ በአገራችን ሰሜናዊ ክፍል የተፈጠሩትን ብሔረተኛ ድርጅቶች በተመለከተ ከጠባብ ብሔረተኝነት ባህሪያቸው የመነጨውን ከለልተኝነት፣ ኢ-ዴሞክራሲያዊና፤ ፀረ-አንድነት ይዞታቸውን፤ "ኢትዮጵያ ቅኝ ገዥ አገር ናት" የሚለውን መሠረተ ቢስ የመገንጠልና የማስገንጠል ማጠየቂያቸውን ስለተቃወማቸው "ዓባይ ኢትዮጵያ" - ታላቋን ኢትዮጵያ - የሚመኝ ትምክህተኛ ድርጅት በሚል ክስ፣ ጦራቸውን የሰበቁበት። ከተቀሩት ብሔረሰቦች ሊነጥሉት ስላልቻሉ፣ ሲፈሩት፣ ተንኮል ሲሸርቡበትና ሊያጠፉትም ሲረባረቡበት የኖሩትና አሁንም ያሉት።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ጥቅም እንታገል፤ ጭቆናን በጋራ አስወግደን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በመመስረት እኩልነትን አረጋግጠን የምንኖርባት አገርን እንመሥርት ብሎ ያቀረበላቸውን ጥሪ ካለመቀበል አልፈው እንደ ወያኔ ዓይነቶቹ ዘረኛ ቡድኖች ከሌሎች ጸረ-አንድነት ሃይሎች ጋር በማበር ኢሕአፓን የማጥፋት ዘመቻን መርጠው ነው የተጓዙት።

ለዓመታት በየአደባባዩ "ኢሕአፓ የለም !" "ኢሕአፓ ጠፍቷል!" እያሉ መጠነ ሰፊ የሆነ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ሲያካሂዱ ከነበሩት የህወሓት መስራችና የጠባብ ብሔርተኛ ቁንጮዎች መካከል ሁለቱ (አባይ ጸሐዬና ስዩም መስፍን) በአገራችን ለተቀሰቀሰው፣ ለተቀጣጠለውና አሁንም ላላባራው ሕዝባዊ እምቢተኝነት/አመፅ ኢሕአፓን ሲከሱ/ተጠያቂ ሲያደረጉ በቅርቡ ተደምጠዋል። ለነዚህ ጀንበር ሳይጠልቅ፤ ጎህ ሳይቀድ ያሉትን ለማይደግሙ ሃሳዊ መሲሃን ያለን ምላሽ አጭርና ግልጥ ነው። "ኢሕአፓ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ የተፈጠረ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ነው"። ኢሕአፓ የደደቢቱንም ሆነ የቤተመንግሥቱን ፀረ-አገርና ፀረ ሕዝብ የሆነውን ወያኔ ጠንቀቶ ስለሚያውቅ፤ እስከወዲያኛው ፀረ-ወያኔ ትግሉን አጠናክሮ ይቀጥላል ነው መልሳችን።

ወያኔ ሲቀየር የሚታያቸው ቢኖሩ ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ ባይ ህሊና ቢስ ተባባሪዎቻቸውና የጸረ-ኢትዮጵያዊው ክፍል ጉዳይ አስፈፃሚዎች ብቻ ናቸው። መሬት ከብነቷን፣ ወያኔም ወያኔነቱን ከቶም የማይቀየርና የማይለውጥ በመሆኑ፤ የወያኔነት ሥጋ-ወደሙ አገርን ማዳከምና መበተን፣ ህዝብን መከፋፈል፣ እርስ በርስ ማናቆርና ታሪክን ማርከስ ነው ።

ህዝባዊ የሆነው የትግል ታሪክ ዛሬም እየታደሰ ነው። እየተደገመ ነው። የትውልድን ወኔ ትውልድ እየተረከበ ነው። ያ "መሬት ላራሹ!" ፤ "ትምህርት ለሁሉም!" ፤ "ዳቦ ለተራበው!" ፤... እያለ ድምፁን ያሰማ የነበረው፤ ያ "የሀገር ክብር ይጠበቅ!፡ ፤ "ፋሽስታዊው አገዛዝ ይወገድ!" ፤ "የሕዝብ ሉዓላዊነት ይረጋገጥ!" እያለ የታገለውና የተሰዋው ትውልድ ተኪ አፍርቷል። ትግሉም ህዝባዊነቱን አስመስክሯል። በወቅቱ

የምናየውና በአገራችን በመካሄድ ላይ ያለው ፀረ-ወያኔ ሕዝባዊ ትግልም ዳግም በሕዝብ ወሳኝ ተሳትፎ ላይ ተመሥርቶ፤ከነጠኞች፣ ከአፋኞች፣ ከከፋፋዮችና ከባእዳን ተጽእኖ ለመላቀቅ የሚደረገውን ትንቅንቅ ተያይዞታል።

ሕዝባዊ ትግል ደግሞ ሂደቱም ሆነ ውጤቱ በሕዝብ ተሳትፎ የሚወሰን ነው። በሂደቱ ጅማሮም ሆነ አጨራረስ የሕዝባዊ አካላት ተሳትፎ አሁንም ለታለመው ግብ ስምረት ወሳኝ ነው። ይህ ደግሞ ዛሬ የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ልባዊ ፍላጎት እንደሆነ እየተንጸባረቀ ያለ ሐቅ ነው። ለዚህ ፍላጎትሥምረት ደግሞ እምነትና ተግባር መዋሀድ አለባቸው። በኢትዮጵያዊነት ማመን፤ በታሪካችን መኩራራትና መኮፈስ፤ በቃላት ብቻ ተለፍፎ የሚቀር ከሆነ ከስሜታዊ ማስታወቂያነት አልፎ ወያኔን ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ፋይዳ አይኖረውም። በማንነት መኩራትንና እምነትን በዕውን ለማስረገጥ ተግባር የግድ ይሆናል። እምነታችንና ኩራታችን ዛሬ የጀግንነትና የአርበኝነት ተሳትፏችንን ይጠይቃል። ለጠላት/ለወያኔ ዛሬም እንደጥንቱ አንበገርም ብለው ያመረሩና "እምቢኝ ለሀገሬ! እምቢኝ ለወገኔ!" የሚሉ ዜጎች ያስፈልጋሉ። ሕዝቡ ዛሬ የጀመረውን የትግል ጎዳና አምርሮና ፀንቶ ጠላትን ከየአቅጣጫው በማስጨነቅ መውጫ መግቢያ ማሳጣት ከቻለ ሕዝባዊ ትግሉ የሚጠይቀውን የጊዜም ሆነ የማንኛውንም ዓይነት መስዋዕትነት ማሳጠር የሚቻል ለመሆኑ በርግጠኝነት መናገር የሚቻል ነው።

የኢሕአፓን የትግል ሥልት፣ የዓላማ ግልጽነት፣ እምነትና ቁርጠኝነት በስልት ለማሽማቀቅ ለሚሞኙ ለብኸርታ እንኳን ቦታም ሆነ መንገድ የሚከፍት ከቶውንም አይደለም። ሊሆንም አይችልም። ለማንኛውም ጸረ-ኢትዮጵያ ሃይላት ሆነ የባዕዳን ፀበል ለተረጨ አፈ ቀላጤዎች ትናንትም አላጎበደደም። ዛሬም አያጎበድድም። ኢትዮጵያችን ዛሬ ለወደቀችበት አዘቅት ያበቃትን አደግዳጊነትም አይቀበልም። እንዲሁም ደግሞ ታሪካዊ መርገም የሆነውን ቡድን አቅም ሰጥተው ለአገር ውድቀት፣ ማኅበራዊ ድቀትና ብሔራዊ ውርደት ያበቁን ኃያላን ተመልሰው መፍትሄ ያመጣሉ በሚል የቀን ቅዥት መዋለል ከቶም አይቃጣውም።

ስለሆነም የሁሉም ነገር ምንጭና መገኛ ሕዝብ ነውና፤ ኢሕአፓ መሠረቱ እድርጎ የተነሳው ሕዝብን ራሱን ብቻ ነው። መሠረታዊና ወቅታዊ ሀላፊነቱም ጊዜው ለጠየቀው ሕዝባዊ ትግል የማታገያ መድረክ ሆኖ ለማገልገል ነው። ዜጎችን በሕዝባዊ ትግሉ ማሳተፍ፤ ትግላቸውን ማቀድና ማቀናበር፤ የፍልሚያውን አቅጣጫ መቀይስና መልክ ማስያዝ፤ ብሎም ለስኬት ይደርስ ዘንድ መንቀሳቀስ የኢሕአፓ ዋና ተግባር ነው። ኢሕአፓ ዛሬ በትግል ጎልምሶ ፤ በትግል ተመክሮን ያካበተ፣ በእሳት የተፈተነ፣ ለባእዳን ያልተንበረከከ ኢትዮጵያዊና ሕዝባዊ ድርጅት ነው። የአገሩንና የህዝብን ጥቅም ከማንምና ከምንም በላይ የሚያስቀድም ለመሆኑ በተግባር ያስመሰከረና ፅናትን የተላበሰ ድርጅት ነው። ይህም ማለት ኢሕአፓ የሕዝቡ አስተማማኝ መታገያ መሣሪያ ነው ማለት ነው። ይህን የሱ የራሱ የሆነውን ርቱዕ መሣሪያ (ድርጅት) ደግሞ ሕዝብ ሳያመነታ ሊጠቀምበት ይገባል።

የዛሬ ሃያ አምስት ዓመት በወርሃ ግንቦት 1983 ዓ.ም የምኒልክን ቤተመንግሥት የተቆጣጠረው ወያኔ ከመነሻው የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪካዊ እሴቶች በትዕቢት እየደመሰሰ፤ የኢትዮጵያዊነት መለያው፤ ክብሩና ብሔራዊ አርማው የሆነውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰንደቅ-ዓላማ እያቃጠለና እየቀደደ ነው በህዝብ ጫንቃ ላይ የተንፈራጠጠው።

ወያኔ ዛሬ በየአቅጣጫው ከህዝብ ተነጥሎና በህዝባዊ አመፅ/ተቃውሞ ተወጥሮ ይገኛል። ለህዝብ ካለው ንቀትና ጥላቻም የተነሳ በሰላማዊ መንገድ ሰብዓዊ መብቱን ለማስከበር ወደአደባባይ የወጣን ሕዝብ ህፃን ሽማግሌ ሳይለይ በቅልብ አግዓዚ ወታደሮቹ አማካይነት ረሽኗል፤ አካለ ስንኩል አድርጓል። ወላጅ እናት ልጇ እሬሳ/አስከሬን ላይ እንድትቀመጥ በማስገደድ ለሰው ልጅ ህሊና የሚሰቀጥጥ ፋሽስታዊ ድርጊት ፈጽሟል። እንዳለፈው የፋሽስቱ የደርግ አገዛዝ ዛሬም ወያኔ በኢትዮጵያ ወጣቶች ላይ ቀይ ሽብር እያካሄደ ይገኛል። ወጣቱን በጅምላ ያሳድዳል፣ ይገድላል፤ ያፍሳል፤ በግብረ-ሰየል ያሰቃያል። ወያኔ ነባር እስርቤቶች አልበቃ ብለውት ወታደራዊ ካምፖችን ከመጠቀም አልፎ አዳዲስ የማሰቃያና የማጎሪያ ሥፍራዎችን በብዛት እየከፈተ ነው። ትምህርት ቤቶች እስርቤቶች ሁነዋል። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ወጣቶች በአረመኔው ዘረኛ የወያኔ አገዛዝ ምሬትና ብሶት የተነሳ ዱሩ ቤቴ ለማለት ተገደዋል። ባለፉት ሃያ ስድስት አረመኔያዊ የአገዛዝ ዘመኑ ወያኔ በህዝብ ላይ ያለውን ቁጥጥር ለማጠናከርና እመቃውንና መብት ረገጣውን ለመቀጠል የሚገለገልባቸው በርካታ ህጎችና ደንቦች መዋቅሮች በገፍ አቋቁሞ በህዝብ ላይ ጭኗል። ህዝቡን መዋሸት የአገዛዙ ድርና ማግ ሆነዋል። ወያኔ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የተጠላ፤ ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ጋር ደም የተቃባ ከመሆኑ የተነሳ በጡንቻው ብቻ በመመካት ገደል አፋፍ ላይ ተነጠልጥሎ እንደቆመ ድንጉጥ ተናካሽ አውሬ መመሰል ይቻላል።

ትናንትና በወያኔ መሪዎችና አጋሮቹ መሰሪ ተንኮል ብሔራዊ አንድነቱን፣ ብሔራዊ ክብሩን መሰረታዊ የሆኑ ዴሞክራሲያዊና የሰብዓዊ መበቶቹን የተገፈፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከቀየውና ከሥራ ገበታው ተፈናቅሎ ለልመና የተዳረገው፤ በገዛ ሀገሩ ስደተኛ የሆነው፤ አርሶ እንዳይበላ ከመሬቱ የተፈናቀለው፤ ነግዶ እንዳይበላ የንግድ ቤቱን እስከነ ፈቃዱ የተነጠቀውና የገበያ አዳራሹ የጋየበት/የተቃጠለበት፤ ለሀገሩና ለክብሩ ድምፁን ከፍ አድርጎ ጭቆናው ይቁም በማለቱ በየአውራ መንገዱ የተደፋው ዜጋ ወያኔን የሚደግፍበት ምን ምክንያት ይኖረዋል?

በመርዘኛ የዘር ጥላቻ ስብከት ጦስ ወገኖቹ ቤት ተዝግቶባቸው በእሳት የጋዩበት፤ አይናቸው እያየ ገደል የተጣሉበት፤ በጭካኔ በስለት የታረዱበት ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወያኔዎችን "ወጊዱ!፡ ብሎ የቁጣ በትሩን አንስቶባቸዋል። ከእንግዲህ ወደፊት እንጂ ወደኋላ የለም ሲል ለወያኔ ቀይ ካርድ አሳይቶታል። መስከረም ሲጠባ ቢገልጡት ወያኔ ያው ወያኔ ነው። በባህሪም በምግባርም ያው እንደወትሮው ፀረ- አንድነት፤ ፀረ ሕዝብ፤ ዘረኛና ፀረ-ዴሞክራሲ ነው። ዛሬም እንደ ትናንቱ ጠባብ ብሔረተኛ ሆኖ በሌላው ላይ ይዘምታል። መርዘኛ ጠባብ በሔረተኝነትን ያስፋፋል። ሀገሪቱን በጎሳ ሸንሽኖ ለሥልጣን ዳረጎቱ ታዳሚዎች እንዳቀራመተ ነው።

ዛሬም እንደትናንቱ እያንዳንዱ ብሔረሰብ ተገነጣጥሎና ተነጥሎ ይኑር የሚለውን የደደቢት ፖለቲካውን የሙጥኝ እንዳለ ነው። አንቀፅና ቁጥር ሰጥቶም ህግ እንዳደረገው ነው ያለው። ዛሬም እንደትናቱ የሕዝብን በነፃ የመደራጀት፤ ሀሳብን በነፃ የመግለፅ፤ ተቃውሞን በነፃ የማሰማት፤ ትክክለኛ ፍትህና ርትዕን የማግኘት፤ ሰርቶ የመኖርና፤ በፈለገበት አካባቢ የመዘዋወር ...ወዘተ. መብቶችን እንደረገጠ ነው። ለዴሞክራሲ፣ ለሰላም፣ ለአንድነትና ለእኩልነት የሚታገሉ የፖለቲካ ድርጅቶች አባላትና ደጋፊዎች ፣ ጋዜጠኖች፣ የማንነትን ጥያቄ ያነሱ የዚህ ወይም የዚያ ብሔረሰብ አባላት፤ ለሃይማኖት መብታቸው የታገሉ ምዕመናን፤ ወያኔን በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ የተቃወሙ አገር ወዳድ ዜጎች ሁሉ የወያኔ የሚስጥርና የይፋ እስርቤቶች ሰለባዎች ሆነዋል።

ዛሬ ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚያደርሰው ግፍና በደል ፅዋው ሞልቶ በመፍሰሱ የተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር ፤ "በቃኝ ግፉ! በቃኝ ዘረኝነቱ!" በማለት ተነስቷል። በደሙ የህይወት መስዋዕትነትም በመከፈል ላይ ይገኛል። ወያኔ ሺህ ጊዜ ቢያላዝን የኢትዮጵያን ሕዝብ ያቄመ ልብ ሊያለዝብ ከቶም አይቻለውም። ሕዝብና ወያኔ ሆድና ጀርባ ከሆኑ ዘመናትን አስቆጥረዋል። የኢትዮጵያ ወጣትም እንግዲህ ወያኔ ከዚህ በፊት ካደረሰበት ግፍና በደል በሺህ እጥፍ የሚልቅ ቀጣይ የሆነ ግፍና በደል እንዲደርስበት ይፈልጋል ማለት ዘበት ነው። የትውልድን ወኔ ትውልድ እየተረከበ ነው። ያ ለማህበራዊ ፍትህና ህዝባዊ መንግሥት ታግሎ የተሰዋው ትውልድ ተኪ አፍርቷል። ተሰዋ እንጂ አልሞተም። የዘረኞችን መንጋ እንደነጋበት ጅብ አጋልጦ ዛሬም ህያውነትን ተላበሰ እንጂ። ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ህዘባዊ ቁጣው ተቀጣጥሏል። አገርን በጋራ ከመገንባት ይልቅ ህዘብን አስተሳስረው የኖሩ ብሔራዊ እሴቶችን መትረው አገርን እንደ ዶሮ ብልት ለመገነጣጠል የተነሱ ጎጠኞችና ተገንጣዮች መረባቸው ተበጣጥሷል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ ላይ ጥርሱን ከነከሰ ቆይቷል። ለዘመናት በወያኔ የደረሰበት ግፍና በደል አስቆጥቶታል። ልቡን ለወያኔ የሚያራራበት፤ ጆሮውን ከፍቶ ወያኔን የሚዳምጥበት ልቦና ከእንግዲህ የለኝም ብሎታል ። በተጠራቀመ በደልና ብሶት ተማሮ በዘረኛው አገዛዝ ላይ ክንዱን አንስቷል። የጎንደርና የጎጃም ህዝብ በወያኔ ላይ ቃታውን ስቧል። በአዲስ ዓመት፤ በአዲስ ዘመን ታሪክ ተደግሟል። በአዲስ ዓመት ለሰላማዊ የሕዝብ ተቃውሞ አምባገነኖች የሚሰጡት ምላሽ ጥይት ጭፍጨፋ መሆኑ በተግባር ታይቷል። ትግሉ መስዋዕትነትን መጠየቁ አይቀሬ እንደመሆኑ ሁሉ፣ ሕዝቡ በወያኔ አገዛዝ ላይ በቀጥታና በብዛት የሚሳተፍበት ትግል ድልን እንደሚቀዳጅ ደግሞ አያጠራጥርም። ይህም ድል ከብዙ የትግል ውጣ ውረድና መስዋዕትነት በኋላ ሊመጣ እንድሚችል ምንም አይነት ጥርጥር የለንም።

የየካቲት 1966ቱ የለውጥ አንቅስቃሴ ድንገት የተከሰተ ቢመስልም፤ ጭቆናና በደል የወለደው፤ ለዓመታት የተደረገውን የሕዝብ ትግል ተንተርሶ የመጣ መሆኑ መረሳት የለበትም። የኢትዮጵያ አርሦ አደሮች አመጽ (የብቸና፣ የስሜን ጃናሞራ እና ሌሎችም አመፆች ያስታውሷል)። የኢትዮጵያ ሠራተኞች ትግል፤ (የምድር ባቡርና የወንጅ) የኢትዮጵያ ተማሪዎች፣ መምህራን አመፅ፤ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እንቅስቃሴ፤ የኢትዮጵያ ጭቁን ወታደሮች አመፅ ፤ በተለየዩ ወቅቶች የተካሄዱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች፤ የፖለቲካ ድርጅቶች ምሥረታ ጥረቶች፤ የታላላቅ ታጋዮች (እንደነ ሀይሉ ገሞራውና ጸጋየ ገ/መድህን-ደብተራው) ...ወዘተ ሁሉ ተጠረቃቅመው ለሕዝቡ ንቃት፤ መነሳሳትና ለሕዝባዊ አመፅ ብሎም ለአብዮት መፈንዳት መሠረት ሆነዋል።

ዛሬ አገራችን የአለችበትን ተጨባጭ ሁኔታ በጥሞና ስንመለከተው ዘረኛውና ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነው ወያኔ ከደቡብ እሰከ ሰሜን ፤ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ በህዝባዊ እምቢተኝነት/አመፅ ተወጥሮ የተያዘበት ሁኔታ ውስጥ እንዳለ እንገነዘባለን። አገራችን ያለችበት አደገኛ ሁኔታ ሁሉንም ዜጋ የሚነካ እንደመሆኑ መጠን በወያኔ የተነጠቀችውን አገር፣ የተደፈረውን ነፃነታችንና ክብራችንን ለማስመለስ መካሄድ ያለበትና ትግሉ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ዜጋ አገራዊ ግዳጅ ሊሆን ይገባል እንላላን። አገርን ከወያኔ ጥፋት ለማዳን፣ ውርደትንና ሥቃይን ለማስወገድ ሁሉም ዜጋ የድርሻውን ማበርከት አለበት። ትግል በተናጠል የተወሰነበትና መስዋዕት መሆን የተበየነበት የተለየ የህብረተሰብ ክፍል ወይም ዜጋ የለም።

ዛሬ በአገራችን በወያኔ አገዛዝ ያልተጎዳ/ያልተበደለ የህበረተሰብ ከፍል ማግኘት ስለማይቻል፣ ሀዝቡን በዋና ዋና ብሔራዊ ጥያቄዎች ዙሪያ አሰባስቦ ማታገልና መታገል መሠረታዊና ተቀዳሚ ተግባር ነው። የመኖር ወይም ያለመኖር ጉዳይም ነው። በዚህ መስክ የሚደረገው ፀረ-ወያኔ ትግልም ከጠበበ የፖለቲካ ፓርቲ (ቡድናዊ) ልዩነቶች ባሻገር ሰፊና አንገብጋቢ በሆኑ ብሔራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ህዝብን ሊያነሳሳና ሊያስተባብር የሚችል መሆን ይኖርበታል። ይህን ስንል ግን "ኦ ሰላም በስምሽ ስንት ግፍ ተሰራ" እንዳለው በሰላምና እርቅ ወይም በሽግግር ስም ገብተው ለሀያ አምስት ዓመት በብሄራዊ ህልውናችን ላይ ከወራሪ ሃይል ባልተናነሰ የዘመቱብንን ማስታወሱ ተገቢ ነው። እንዲሁም ከራሱ አልፎ መሬታችንን፣ ዳር ድንበራችንንና ብሔራዊ ክብራችንን የደፈረውንና ያስደፈረውን ታሪካዊ መርገም (ወያኔ) ነብስ ሊዘሩለት፣ በተቃዋሚ የድርጅት መሪነት ወይም በታዋቂ ምሁራን ሽፋን የተዘጋጁ ክፍሎችን ከወያኔ ጋር አዳቅለው አገዛዙን ለማስቀጠል፤ የ1983-ኡን የለንደኑን አይን ያወጣ ጣልቃ ገብነት ዳግም አውን ለማድረግ፣ ከመቶ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ አየሸረቡ እንዳሉ ለማየት የፖለቲካ ልሒቅ መሆንን አይጠይቅም።

ስለዚህ ብዙ ሺህ ወገኖቻችን ውድ ህይወታቸውን የከፈሉበትና ገናም የሚከፍሉበት አገር አድን ትግል ዳግም አንዳይነጠቅ መከላከል የሚቻለው፣ ሀዘባዊ ትግሉ ወያኔንና ለጊዜው ተመሳስለው በመሰለፍ የተገንጣይ ዓላማቸውን ለማሳካት የሚያደቡ ቡድኖች ላይ ድልን ሲቀዳጅ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ የህዝብን ይሁንታ ያገኘ፤ ሕዝብ የሥልጣን ምንጭ የሚሆንበት፤ የብዙሃኑ ድምፅ እሚገዛበትና የአናሳው መብት የሚጠበቅበት/የሚከበርበት፣ በሕግ ፊት አኩልነት፣ ነፃና ፍትሃዊ የሆነ የምርጫ ሕግ የሚከበርበት፤ ለመሠረታዊ መብቶች ዋስትና የሚሰጥበት፣ የመንግሥት ሥልጣን የሚወሰንበትና የህዝብን ሉዓላዊነት ለጠበቀ (የህዝብ፣ በህዝብ፣ ለህዝብ ለሆነ) ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት የሚጥል የሽግግር መንግሥት ሲረከበው ብቻ ነው።

የሚያታግሉን ወቅታዊ መፈከሮች ብዙ ናቸው። የሕዝብ ብሶት ከመቸውምጊዜ በላይ በአስከፊ ደረጃ ላይ ይገኛል። ይህን የሕዝብ ቁጣ አቅጣጫ እንዲይዝ ማድረግ ያስፈልጋል። ሕዝቡን በወቅታዊ መፈከሮች ዙሪያ በማሰባሰብ/በማደራጀት፤ ትግልን በትግል በማጠናከር፤ ሕዝባዊ አመፁን በማቀጣጠልና በማስተሳሰር በሂደት የሚታዩ ድክመቶችን በማስወገድና ህዝባዊ ተሳትፎን በማዳበር የአገዛዙን እድሜ ማሳጠር ይቻላል። የወያኔ ጭፍጨፋ፣ ድንፋታና ደርሶ አልበገር ባይነት የተለመደ የአምባገነኖች/የፋሽስቶች ባህሪ መሆኑ የታወቀ ነው። ሕዝብ ተባብሮ እምቢ ካለና፤ በሁለገብ መንገድ አንዱን የትግል ሥልት በሌላው እንዲታገዝ እያደረገ፤ ቀጣይ በሆነ ትግል ወያኔን ካዋከበና፣ ቆርጦ ከታገለ የድሉ ቀን ሩቅ እንደማይሆን መናገር ይቻላል።

ብሔራዊ ህልውናውና ጥቅሙ ሲነካ የማይታገል ሕዝብ ራሱን ለብዝበዛና ለባርነት ያመቻቸ ሕዝብ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም። እንደዚሁም በዚህ ወሳኝና አገር አድን ትንቅንቅ ወቅት፣ ሁኔታው እስኪለይለት በሚል ደካማ መንፈስ ከትግሉ ወጥቶ ዳር መቆም፣ የወያኔን ፀረ-ሕዝብ እርምጃዎች ከመደገፍ ተለይቶ አይታይም ቢባል ከእውነት የራቀ አይደለም። ነግ በእኔ ሳይሉ የሌላውን ወገኑን ስቃይ አላይም ማለትና የማይቀረውን ውርደት መጠበቅ ምን ትርጉም ሊሰጠው ይገባል? ጠላት ገና ሲያነጣጥር መቅደም እንጂ ከተመቱ በኋላ መላቀሱና ከንፈር መምጠጡ ምንም የሚሰጠው ፋይዳ የለም። ለዚህም ነው ኢሕአፓ ያኔ ገና ከጥዋቱ፣ ወያኔ ከፍጥረቱ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ኢትዮጵያ ነው፤ እንታገለው ያለው። ዛሬም የተለወጠ

አንዳችም ነገር ስለሌለ፣ ፀረ-ወያኔው ትግል (አገራዊው ትግል) ጠንክሮ ይቀጥል ሲል ኢሕአፓ ዳግም ጥሪውን እያስተጋባ የሚገኘው።

አዲሱ ዓመት፣ ህዘባችን ለመብቱና ለነፃነቱ ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ የተንቃነቀበት፣ የተደፈረ ብሔራዊ ክብሩንና ህልውናውን ሊያስከብር ቆርጦ የተነሳበት፣ የወያኔን አምስት ለአንድ ሰንሰለት በጣጥሶ የወጣበት፣ የጎሳ ከልልን ሺሮ አንድነቱን በደሙ ያበሰረበት፣ የደደቢቱን ባንዲራ አውርዶ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርጎ ያውለበለበበት በመሆኑ፣ ለጠላቶቹ ሃፍረትን ለወዳጆቹ ትልቅ የነፃነት ጮራን አብርቷል። ይህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ተስፋና የትግል መነሳሳት በሁለገብ ስልቱ ጉልበት አያገኘ፣ አየሰፋና ግለቱ እጨመረ እንደሚመጣና የወያኔን የገማ የገለማ ዘረኛ አገዛዝ ዳግም አንዳይከሰት አድርጎ የሚቀብርበት ጊዜም እንደሚሆን ግልጽ ነው። ይህ እየተጫጫሰ ያለ ህዝባዊ ትግል ጎምርቶ ለድል አንዲበቃ፣ ሚናችን መሆን ያለበት፣ በሌሉበት አለን እያሉ በቀቢፀ-ተስፋ እንደሚነግዱት ሳይሆን፣ ድርጅታዊም ሆነ የህሊና ነፃነት ያላቸው የሀገሪቱ የቁርጥ ቀን ልጆች በህዝብ መሀል ሆነው፣ እስራቱን፣ ሞቱን፣ ረሃብና ጥማቱን ተጋርተው ታግለው ሊያታግሉት ይገባል። ይህ ሲሆን ብቻ ነው መተባበር ዕውን የሚሆነው። ህብረት/ግንባርም ከዚሁ የትግል ሜዳ የሚፈጠር አንጅ ከላይ ወደታች የሚጭኑት ፅላት አይደለም። ኢሕአፓ አገር በታኝና ትውልድ ገዳይ የሆነውን የወያኔ አገዛዝ ለማስወገድ እየተደረገ ያለውን ሕዝባዊ ትግል ለማጠናከር፣ በጋራ በመታገልም የበኩሉን ሀገራዊ ግዴታ ለመወጣት ህዝባዊና አገራዊ ጥያቄዎችን አንግቦ ትግሉን ቀጥሏል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

በተባበረትግልወያኔይወድቃል !!